የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፳፱ኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.27
ADDIS ABABA 6th July, 2023

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፱/፪ሺ፲፭ ዓ.ም

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ......................ገጽ ፲፬ሺ፯፻፸

Content

Proclamation No.1289/20 23

Agricultural Production Contract Proclamation ..........................................Page 14,770

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፱/፪ሺ፲፭

### የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የግብርና ምርት ጥራትን፣ የአመራረት ቅልጥፍናንና ተወዳዳሪነትን እንዲሁም የግብርና እና አግሮ- ኢንዱስትሪ ተመጋጋቢነትን በማሳደግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ወሳኝ በመሆኑ፤

የግብርና ምርት አምራቾችን ለገበያ የሚሆን የግብርና ምርቶችን ወደ ማምረት በማሸጋገር የግብርና ምርቶችን ከሚያዘጋጁ፣ ከሚያቀነባብሩ፣ እሴት ከሚጨምሩ አግሮ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ከትላልቅ ገዥዎች ጋር ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስር መፍጠር ወሳኝ በመሆኑ፤

በሥራ ላይ ያሉት ሕጎች የግብርና ምርት ውልን ልዩ ባሕሪያት በተሟላ መልኩ የማያስተናግዱ በመሆናቸው የግብርና ምርት ውልን በመጠቀም ማምረት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችሉ የዕውቀትና ክህሎት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የገበያ ትስስር የሚፈጠርበት የአምራች እና የአስመራች ግንኙነት በተሟላ የሕግ ማዕቀፍ የሚመራበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) እና (፮) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1289/2023

### A Proclamation to provide for Agricultural Production Contracts

**WHEREAS**, it is key in improvements in product quality, production efficiency, agricultural production competitiveness and l linkage to agro-industries is akey pillar to realize structural economic transformation;

**WHEREAS**, it is critical to create market linkage between agricultural producers and processors, value adding agro-industries and larger buyers in a sustainable manner by transforming them to produce for market;

**WHEREAS**, the existing Laws do not adequately address the particular nature of agricultural production contracts, it becomes necessary to put a system in place that guarantees a producer-contractor relationship led by a comprehensive legal framework and ensures knowledge, skill, and technology transfer as well as market linkages;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1 & 6) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 145 00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

CamScanner

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፱/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የግብርና ምርት" ማለት በጥሬው ተመርቶ ወይም ተመርቶና ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የእጽዋት፣ የእንስሳት እና የዓሳ ዘርና ምርት እንዲሁም የተቀነባበረ መኖ ነው፣

፪/ "እንስሳት" ማለት የዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ የጋማ ከብት፣ ግመል፣ ዶሮ፣ ንብ፣ ዓሣ፣ የሐር ትል፣ አሳማ፣ ሌሎች እና ወደፊትም ሊላመዱ የሚችሉትንም ያጠቃልላል፣

፫/ "ዕፅዋት"፡ ማለት የብርዕ፣ የአገዳ፣ የቅባት፣ የጥራጥሬ፣ የአትክልት፣ የፍራፍሬ፣ የስራስር፣ የመኖ፣ የቅመማቅመም፣ በህግ ያልተከለከለ አነቃቂ፣ የኢንዱስትሪ እና ሌላ የተላመደ ሰብልን እንዲሁም ደንና የደን ውጤትን ያጠቃልላል፣

፬/ "የግብርና ምርት ውል" ማለት በግብርና ምርት አምራች እና አስመራች መካከል የሚደረግ ስምምነት ሆኖ ውልን በሚመዘግብ አግባብ ያለው አካል የተመዘገበ ነው፣

፭/ "አስመራች" ማለት የግብርና ምርትን ለማስመረት ከአምራች ጋር ውል የሚገባ፣ የኢንቨስትመንትና የንግድ ፈቃድ ያለው ወይም የህብረት ሥራ ማህበር ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ ሰው ነው፣

፮/ "አምራች" ማለት የይዞታ መሬት ያለው ወይም ማሳ ተከራይቶ የግብርና ምርት ለማምረት ከአስመራች ጋር ውል የሚገባ ሰው ነው፣

፯/ "የተቀናጅ ውል" ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ አስመራች የራሱ ይዞታ ኖሮት የሚያመርት እና ከሌሎች የግብርና ምርት አምራቾች ጋር ለተጨማሪ የግብርና ምርት ማምረት የሚያደርገው ስምምነት ነው፣

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Agricultural Production Contract Proclamation No.1289/2023"

### 2. Definitions

unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ "Agricultural Produce" means processed feed, seed,breed; of plant, animal and fish and their product in a raw or produced and processed form;

2/ "Animal" means cattle, sheep, goat, draft animal, camel, chicken, bee, fish, silkworm, pig, any others those that might be domesticated in the future;

3/ "Plant" means cereals, pulses. oil crops, vegetables, fruits, root crops, spices, forage crops, non-banned stimulants, industrial crops, forest & forest products and other cultivated crops;

4/ "Agricultural Production Contract" means an agreement between agricultural produce Contractor and Producer that is registered by an appropriate body to register contracts,

5/ "Contractor" means any person with investment & trade license or an eligible cooperative who enters into a contractual agreement with a Producer for agricultural production;

6/ "Producer" means any person who has his own holding or rents farm and enters into contract with a contractor for agricultural production;

7/ "Out-Grower Contract" means a kind of agricultural production contract where the contractor himself is a producer on his holdings and enters into an agreement withother agricultural producers for additional agricultural production.

፰/ "የተማከለ ውል" ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ አስመራች የራሱ የሆነ የማምረቻ ይዞታ ሳይኖረው አምራቹን እየደገፈ ከአምራቹ ጋር የግብርና ምርት ለማስመረት የሚያደርገው ስምምነት ነው፡

፱/ "የባለብዙ ተዋንያን ውል" ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ አስመራች እና አምራች በበጎ ፈቃዳቸው በሦስተኛ ወገን ድጋፍ እና ማስተባበር የሚከናወን የግብርና ምርት የማስመረት ስምምነት ነው፡

፲/ "የአገናኝ ውል" ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ በአምራቹ ፈቃድ አግባብነት ያለው ሰው አምራቹን ወክሎ ከአስመራቹ ጋር የሚያደርገው ስምምነት ነው፤

፲፩/ "ሦስተኛ ወገን" ማለት በአስመራችና በአምራች መካከል በሚካሄድ የግብርና ምርት ውል ሂደት በፈቃዳቸው ድጋፍ የሚሰጥ ሰው ነው፤

፲፪/ "ግብዓት" ማለት ለግብርና ምርት ማሳደጊያ የሚውል ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ፀረ ተባይ፣ ፀረ አረም፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ የፋይናንስ አቅርቦት እና ሌሎች የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ያካትታል፤

፲፫/ "የቴክኒክ ድጋፍ" ማለት የግብርና ምርትን በማምረት ሂደት የሚጠይቀውን የዕውቀትና የክህሎት ሥልጠና እና የምክር አገልግሎት ነው፤

፲፬/ "አግባብ ያለው አካል" ማለት አዋጁን እና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎች ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው የግብርና ሚኒስቴር ወይም በክልል ግብርና የሚመለከተው የመንግስት ተቋም ነው፤

፲፭/ "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤

፲፮/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀፅ 47 መሠረት ማንኛውም ክልል ሲሆን፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን፣ ድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

8/ "Centralized Contract" means a kind of agricultural production contract where the contractor does not have his own holding but enters into an agreement with producer while supporting him;

9/ "MultipartiteContract" means a kind of agricultural production contract between the contractor and the producer with active support & coordination of a third party based on good will of contracting parties;

10/ "Intermediary Contract" means a kind of agricultural production contract made by person on behalf of the producer with the contractor;

11/ "Third Party" means a person who provides support in agricultural production contract processes between the producer and the contractor;

12/ "Input" means improved seed, fertilizer, pesticide, herbicide, technical assistance, financial access, and any agricultural technology necessary for enhancing production;

13/ "Technical Assistance "means any knowledge or technical skills or training necessaryinthe process of agricultural production;

14/ "Appropriate Authority" means the Ministry of Agriculture or respective regional organ responsible for Agriculture, upon which the powers and duties are vested under the provisions of this proclamation; and its regulations or directives issued for the implementation of this proclamation.

15/ "Ministry" means the Ministry of Agriculture

16/ "Region" means any region referred to under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa City Administration, Dire Dawa Administration. ;

CamScanner

፲፯/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡

፲፰/ በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በማንኛውም አስመራች፣ አምራች፣ ሶስተኛ እና አግባብ ባለው አካል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የግብርና ምርት ውል መነሻ ሀሳብ አቀራረብና ይዘት</u>

**፬. <u>አቀራረብና የድርድር አግባብ</u>**

፩/ የግብርና ምርት ውል አመሰራረት የሚጀምረው አስመራቹ ወይም አምራቹ በሚያቀርበው የውል ሀሳብ መነሻነት ሊሆን ይችላል፡፡

፪/ የግብርና ምርት ውል መነሻ ሀሳብ በጽሁፍ ወይም በቃል ሊቀርብ ይችላል፡፡

፫/ የውል የመነሻ ሀሳብ የምርቱን ዓይነት፣ ዋጋን፣ የአከፋፈል ሁኔታን፣ መጠንን፣ የጥራት ደረጃን፣ የጊዜ ገደብን፣ የማከማቻ መጋዘንን፣ የማስረከቢያ ቦታን፣ የሚያስፈልግ ድጋፍን፣ የክትትልን እና ሌሎች የተዋዋዮች ውሳኔ ሊደግፉ የሚችሉ መረጃዎች ይጨምራል ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀው ቢኖርም ማንኛውም መንግስታዊ ተቋም ወይም መንግስታዊ ያልሆነ የልማት ድርጅት የግብርና ምርት ውልን አስመልክቶ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ሀሳብ ማቅረብ ወይም ማመቻቸት ይችላል፡፡

፭/ የውሉ ሀሳብ የቀረበለት ተዋዋይ ወገን የውሉን ሁኔታዎች በአግባቡ ለመረዳት በቂ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል፡፡

፮/ በግብርና ምርት ውል ድርድር ሂደት ተዋዋይ ወገኖች በሶስተኛ ወገን እገዛ ሊደረግላቸው ይችላል፡፡

17/ "Person" means a natural or juridical person;

18/ under this proclamation, an expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Proclamation shall be applicable on any contractor, producers, third party and appropriate authority..

## <u>PART TWO</u>

## <u>FORMATION AND CONTENT</u>

**4. <u>Initiation and Negotiation</u>**

1/ The formation of agricultural production contract can be initiated through contract offer by either the Contractor or the Producer.

2/ The initial offer shall be in either writing or oral.

3/ Contract initial offer may include information like produce type, price, terms of payment, quantity, quality standard, deadlines, storage, place of produce handover, kind of support to be provided, tracking and any other information necessary to support all parties to make decision.

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, any government institution or non governmental development organization may create an awareness, initiate and facilitate an offer .

5/ The offeree shall be given sufficient time to review and understand the terms of the contract.

6/ Both parties may be assisted by a third party in the process of agricultural production contract negotiations.

## ፭. <u>የግብርና ምርት ውል አዘገጃጀት</u>

፩/ የግብርና ምርት ውል በማያሻማ ሁኔታ በጽሁፍ መዘጋጀት አለበት፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች የግብርና ምርት ውላቸውን በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ሊያዘጋጁ ይችላሉ፣ አንዱ ግን የክልሉ የሥራ ቋንቋ መሆን አለበት፡፡

፫/ ውሉ ከአንድ በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ተዘጋጅቶ የትርጉም ልዩነት ሲከሰት ውሉ የተፈፀመበት ክልል የሥራ ቋንቋ ገዥ ይሆናል ፡፡

፬/ የግብርና ምርት ውል ቢያንስ በሦስት ምስክሮች ፊት መፈረም አለበት፣ ከምስክሮች አንዱ አግባብ ያለው አካል ተወካይ ሊሆን ይገባል፡፡

፭/ የግብርና ምርት ውል ውል ለመመዝገብ ሥልጣን በተሰጠው አካል መመዝገብ አለበት፡፡

፮/ ውሉ ከግብርና ምርት ውል ድንጋጌዎች ውጪ ሌሎች ሰነዶችን የሚጠቅስ ሲሆን የተጠቀሱት ሰነዶች ከተፈረመ የውሉ ቅጂ ጋር የውሉ አካል ሆነው ውል ለመመዝገብ ሥልጣን ለተሰጠው አካል መቅረብ አለባቸው፡፡

## ፮. <u>የግብርና ምርት ውል ይዘት</u>

የግብርና ምርት ውል ቢያንስ የሚከተለው ይዘት ሊኖረው ይገባል፡-

፩/ የአምራቹ እና የአስመራቹ ሙሉ ስም እና አድራሻ፣

፪/ አስመራቹ የግል አምራች ድርጅት ከሆነ የኢንቨስትመንትና የንግድ ፈቃድ ቁጥር፣

፫/ አስመራቹ የመንግስት የልማት ድርጅት ከሆነ የተቋቋመበት ሕግ እና የንግድ ፈቃድ፣

፬/ አስመራቹ ህብረት ሥራ ማህበር ሲሆን ሕጋዊ ሰውነት ያገኘበት የምስክር ወረቀት፣

፭/ የአምራቹ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ሕጋዊ የመሬት ኪራይ ውል፣

## 5. <u>Agricutural Production Contract Form</u>

1/ An Agricultural Production Contract shall be made in writing using simple and standard language.

2/ The parties may draw up their contract in one or more languages, one of which is the working language of the Regional S tate.

3/ Where the contract is drawn in more than one language, the version with the Region's working language shall be the governing in case of discrepancy.

4/ The Contract shall be attested by at least three witnesses, one of whom shall be a representative of the appropriate authority.

5/ The Agricultural Contract shall be registered by the appropriate document Authentication and Registration Authority.

6/ Where the text of the contract refers to documents and texts other than the provisions of the contract, such documents shall be attached to the signed copy of the contract for registration upon submission to the appropriate document's authentication and registration authority.

## 6. <u>Content</u>

An Agricultural Production Contract shall at least include the following:

1/ The names and addresses of the Producer and the Contractor;

2/ Investment and business license reference number, if the contractor is a private producer company;

3/ An establishment regualtion and trade license, for public owned enterprise contractors.;

4/ Registration Certificate, for cooperative contractors;

5/ For producers, Land Owner Certificate or legal land rent contract ;

CS CamScanner

፮/ የግብርና ምርት ውሉ ዓላማ፣

፯/ የማሳው ወይም የማራቢያ ቦታ ስፋትና አዋሳኞች ወይም የሚራባው ብዛት፣

፰/ የአምራቹ እና የአስመራቹ መብትና ግዴታዎች፣

፱/ የምርት ዓይነት፣ ጥራትና የመጠን መግለጫ መስፈርቶች፣

፲/ የግብዓት እና የምርት ዋጋ አወሳሰን፣

፲፩/ የማጓጓዣ ሥርዓትና የወጪ አሸፋፈን፣

፲፪/ የቴክኒክ ድጋፍ ዓይነቶች፣

፲፫/ እንደአግባብነቱ የአዳቃዮች እና የአዕምሮ መብት ባለቤትነትን የተመለከቱ ድንጋጌዎች፣

፲፬/ ውሉ እንዳይፈፀም ማድረግ የሚችሉ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች፣

፲፭/ የተዋዋይ ወገኖች ወራሾች ወይም ተተኪዎች መብትንና ግዴታን ስለማስተላለፍ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፣

፲፮/ የግብርና ምርት ውሉ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣ ስለሚሻሻልበት ወይም ስለሚቀየርበት፣ ስለሚቋረጥበት ሁኔታዎችና ሥነ-ሥርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፣

፲፯/ አለመግባባቶችን መፍቻ መንገዶች፣

፲፰/ በምርት ውሉ መሰረት የምርቱ ጥራትና መጠን በመቀነስ ወይም በመጨመር ልዩነት ቢፈጠር የዋጋ ሥሌት ማስተካከያ ስለሚደረግበት፣

፲፱/ የግብርና ምርት ውሉ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ፡፡

## ክፍል ሦስት

## የግብርና ምርት ውል ዓይነቶች፣ የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች

### ፯. የግብርና ምርት ውል ዓይነቶች

በዚህ አዋጅ የግብርና ምርት ውል ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

6/ The objective of the contract;

7/ Agricultural Production site and its boundaries or quantity of agricultural produce;

8/ Rights and Obligations of the Producer and the Contractor;

9/ Type, quality and quantity of agriculture produce, and descriptions of unit of measurement;

10/ Pricing mechanism of agriculture produce and input;

11/ System of transportation and related costs;

12/ Types of technical supports;

13/ As required legal provisions related to Breeder` and intellectual property rights;

14/ Provisions specifying the causative events that can be considered as force majeure;

15/ Provisions on inheritors or substitutes of contracting parties and transfer of obligations & rights;

16/ The duration or validity date of the contract, and conditions as well as procedures of agricultural production contract renewal, amendment, alteration or terminations;

17/ Dispute resolution mechanisms;

18/ Price amendments when quality & quantity of the agricultural produce exceeds or drops below agreed quantity and standards respectively; and

19/ The date and place of signature by the parties to the Contract.

## PART THREE

## TYPES OF AGRICULTURAL PRODUCTION CONTRACTS, RIGHTS AND OBLIGATIONS OF PARTIES

### 7. Types of Agricultural Production Contracts

According to this Proclamation, the following are the types of Agricultural Production Contracts:

CamScanner

፩/ የተቀናጀ ውል፤

፪/ የተማከለ ውል፤

፫/ ባለብዙ ተዋንያን ውል፤እና

፬/ የአገናኝ ውል፡፡

## ፰. የአስመራቹ መብትና ግዴታዎች

፩/ አስመራቹ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በሰጠው ግብዓት እና የቴክኒክ ድጋፍ መሠረት የማምረት ሥራው ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ የአምራቹን የማምረቻ ቦታ በሥራ ሰዓት የመከታተል፤

ለ/ በግብርና ምርት ውሉ በተመለከተው ቦታ፣ ጊዜ፣ የምርቱን ጥራትና መጠን አረጋግጦ የመረከብ፤

ሐ/ በውሉ በተጠቀሰው መሠረት የግብርና ምርትን ጥራት የሚያስጠብቁ ግብዓቶች አቅርቦ አምራቹ የጥራት ደረጃን ያላሟላ የግብርና ምርት ሲያቀርብ ያለመረከብና አምራቹን በሕግ ተጠያቂ የማድረግ፡፡

፪/ አስመራቹ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) በተሰማራበት መስክ ሕጋዊ የኢንቨስትመንት እና የንግድ ፈቃድ ወይም የህብረት ሥራ ማህበር ሕጋዊ ሰውነት ያለው ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት መሆኑን የሚያረጋግጥ የተቋቋመበት ሕግ የማቅረብ፤

ለ) በግብርና ምርት ውሉ መሠረት አግባብነት ያላቸውን የግብርና ግብዓቶች እና የቴክኒክ ድጋፍ ለአምራቹ የማቅረብ፤

ሐ) አምራቹ መረጃ እንዲይዝ ክትትልና የቴክኒክ ድጋፍ የማድረግ፤

መ) በግብርና ምርት ውሉ መሠረት ክፍያ በወቅቱ የመፈፀም፤

1/ Out-grower Contract;

2/ Centralized Contract;

3/ Multipartite Contract; and

4/ Intermediary Contract.

## 8. General Rights and Obligations of the Contractor

1/ The Contractor shall have the following rights:

a) To enter into the production farm of the producer to follow up whether the production process is undergoing according to provided input and technical support;

b) as indicated in the agricultural production contract to receive agricultural produce at agreed place & time, confirming its quality and quantity;

c) to reject any substandard product brought from the producers and make him accountable provided that he supplied the necessary inputs, according to the contract, that ensure agricultural produce quality.

2/ The Contractor shall have the following obligations:

a) To submit an investment and trade license or cooperative registration certificate or public enterprise establishment regualtion in areas of his engagement;

b) to ensure the delivery of input and technical support to the Producer as agreed in the agricultural production contract;

c) to track and monitor the producer to compile the required information are documented;

d) effect payment to the Producer at time agreed in the Agricultural Production Contract;

CamScanner

ሠ) በግብርና ምርት ውል መሠረት ለማስመረት ብቁ ስለመሆኑ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው ቢሮ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማቅረብ የሚችል፣ ዝርዝር አፈፃፀሙ በሚኒስቴሩ መመሪያ ይገለፃል፡፡

## ፱. የአምራቹ መብትና ግዴታዎች

፩/ አምራቹ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ከአስመራቹ በውሉ መሠረት ግብዓት እና ክፍያ የማግኘት፣

ለ) በግብርና ምርት ውሉ መሠረት ከአስመራቹ የሚሰጠውን የግብዓት ዓይነት፣ ጥራትና መጠን በወቅቱ አረጋግጦ የመረከብ እና የመጠቀም፣

ሐ) የሚረከበውን ግብዓት ጥራትና መጠኑን በማረጋገጥ ሂደት የሶስተኛ ወገን ወይም አግባብ ያለው አካል ድጋፍ፣

መ) የቴክኒክ፣ስልጠናና የምክር አገልግሎት ከአስመራቹ የመቀበል፡፡

፪/ አምራቹ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) በውሉ መሠረት የግብርና ሥራ ወቅትን ተከትሎ ወደ ማምረት ተግባር የመግባት፣

ለ) በውሉና በምክረ-ሀሳቡ መሠረት ወቅታዊ የማምረት ስራዎች የማከናወን፣

ሐ) በአስመራቹ ድጋፍ መረጃ የመያዝና የመስጠት፣

መ) የምርት ጥራት የሚያሻሽሉና ብክነትን የሚቀንሱ ተግባራትን የማከናወን፣

ሠ) በውሉ መሠረት ምርቱን በተገለጸው ቦታ፣ ጊዜ፣ ጥራትና መጠን አረጋግጦ ለአስመራች የማስረከብ፡፡

e) submit a competency of certificate issued by the Ministry or an appropriate Authority that assures his competence to engage in agricultural production contracts; particulars shall be prescribed in the Ministry Directive.

## 9. Rights and Obligations of the Producer

1/ The Producer shall have the following rights:

a) to get input and payment from the contractor based on the contract;

b) to confirm the type, quality and quantity of agricultural input provided by the Contractor at delivery and comply to agreed applications;

c) to get support from a third party or an appropriate authority in assuring input quality and quantity;

d) to get technical, training and advisory support from the contractor.

2/ The producer shall have the following obligations:

a) Enter to production activity following the appropriate agricultural season indicated on the contract;

b) To carry out the necessary seasonal agricultural production activities, according to the contract;

c) With support of the contractor to document the necessary information;

d) take appropriate measures that enhance quality of agricultural produce and minimize losses;

e) ensure delivery of agricultural produce at agreed place and time with the quantity and quality specified in the agricultural production contract.

CamScanner

## ፲. የግብርና ምርት ዋጋ፣ የክፍያ ዘዴ እና አከፋፈል

፩/ ተዋዋይ ወገኖች በውሉ የሚሸፈነውን የግብርና ምርት ዋጋ የማምረቻ እና ተዛማጅ ወጪዎችን ይወስናሉ፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች የግብርና ምርቱን ጠቅላላ ዋጋ ወይም የነጠላ ዋጋ ክፍያ ስሌት በግልፅ ማስፈር አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በውል ከተገለጸው የጥራት ደረጃ በመቀነስ ወይም በመጨመር ልዩነት ቢፈጠር የዋጋ ሥሌት ማስተካከያ በውሉ በግልፅ ማስቀመጥ አለባቸው ፡፡

፬/ ተዋዋይ ወገኖች የግብርና ምርቱን ዋጋ አከፋፈል እና የክፍያ ጊዜ በግልፅ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

፭/ በግብርና ምርት ውል የምርትና ግብይት ግንኙነትን ዘላቂነት ለማረጋገጥ በምርት ርክክብ ጊዜ የምርት ገበያ ዋጋ በውል ከተገለጸው በላይ ከፍ ወይም ዝቅ ያለ እንደሆነ ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በድርድር የዋጋ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ በሚኒስቴሩ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፮/ አስመራች በውል በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የተረከበውን የምርት ዋጋ ድምር ተቀናሽ የሚሆን የግብዓት ዋጋና ቀድሞ ለአምራች የተሰጠ ቅድመ ክፍያ ካለ ተቀናሽ በማድረግ ለአምራች በአቅራቢያው በሚገኝ ባንክ በስሙ በከፈተው የባንክ ሂሳብ በኩል ወይም እውቅና ባለው ሌላ የገንዘብ አስተላለፊ በኩል ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

## ፲፩. የግብርና ምርት መጠንን ስለመወሰን

ተዋዋይ ወገኖች፡-

፩/ የግብርና ምርቱን አማካይ መጠንና መለኪያ በግልፅ መወሰን አለባቸው፡

፪/ በውል ከተመለከተው የምርት መጠን ለመቀነስ ወይም ለመጨመር መንስዔ ሊሆኑ የሚችሉ ክስተቶችና የውል ተፈፃሚነት ደረጃ በግልጽ ድንጋጌዎች በውሉ ውስጥ ማካተት አለባቸው፡፡ ዝርዝሩ በሚኒስቴሩ መመሪያ ይወሰናል፡

## 10. Price, Mode, and Term of Payment of Agricultural Produce

1/ The parties shall clearly state, in the contract, the price of an agricultural produce, cost of production, and other related costs.

2/ The contracting parties shall clearly specify either the total or unit price of the Agricultural Produce.

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the parties shall state the basis for price revision in a causative event where quality of the agricultural produce either become below or above of what has been agreed in the contract.

4/ The parties shall clearly specify mode and time of payment for the price of the agricultural produce.

5/ The parties may agree to renegotiate on price when escalations occur at time of agricultural produce delivery, above or below the price indicated on the agricultural production contract, considering equity and long-term interest of both parties. particulars shall be prescribed in the Ministry Directive;

6/ As indicated on the Agricultural Production Contract, the Contractor shall deposit payments, through the nearest bank account of the Producer or through eligible money transfer, after receiving the agricultural produce while deducting price of input, and other advance payments made to the Producer.

## 11. Specifying Quantity of Agricultural Produce

The parties shall:

1/ clearly determine average quantity and units of measurement of the agricultural produce;

2/ clearly determine phenomena that might cause increase or decrease of quantity of agricultural produce to either above or below the agreed quantity and effects thereof on the enforcement of the

CS CamScanner

፫/ የግብርና ምርቱ መጠንና መለኪያው በበቂ ሁኔታ ተዘርዝሮ ያልተቀመጠ እንደሆነ በድርድር ለመወሰን ይችላሉ፡፡

**፲፪. <u>የግብርና ምርት ጥራትን ስለመወሰን</u>**

፩/ ተዋዋይ ወገኖች የምርት ጥራት ደረጃና ማረጋገጫ መንገዶችን በግልፅ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምርት ጥራት መጓደል መንስዔ ሊሆኑ የሚችሉ ክስተቶችና የውል ተፈጻሚነት ደረጃ በግልፅ ድንጋጌዎች በውሉ ውስጥ መካተት አለባቸው፡፡ ዝርዝሩ በሚኒስቴሩ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች እንደ አግባብነቱ የማሸጊያ፣ የምርት የጥራት መግለጫ ደረጃዎችን እና የማሸጊያ ወጪዎችን ማን እንደሚሸፍን ጭምር በውሉ በዝርዝር ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

**፲፫. <u>የግብዓት አቅርቦትና ዋጋ አወሳሰን</u>**

፩/ አስመራቹ የሚያቀርበውን የግብዓት ዓይነት፣ ጥራትና መጠን፣ የርክክብ ጊዜ፣ ቦታ፣ የማጓጓዣ መንገድና ዋጋ በግልፅ በግብርና ምርት ውሉ ላይ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀው ቢኖርም አስመራች ለአምራች የሚያቀርበው የግብዓት ዋጋ በወቅቱ የአካባቢ ገበያ ከሚገኝ ተመሳሳይ ግብዓት ዋጋ መብለጥ የለበትም፡፡

፫/ አስመራች ለግብዓት መግዣና ሌሎች ወጪዎች የሚሆን በጥሬ ገንዘብ ወይም በሌሎች የመክፈያ አማራጮች ቅድመ ክፍያ ሊከፍል ይችላል፤ ሆኖም መጠኑ በምርት ውሉ ከተመለከተው የአጠቃላይ ምርት ዋጋ መብለጥ የለበትም፡፡

agricultural production contract. particulars shall be prescribed by the Ministry Directive;

3/ If parties fail to clearly specify the quantity and measurement unit of the agricultural produce, they can decide upon negotiations.

**12. <u>Specifying Quality of Agricultural Product</u>**

1/ The parties shall clearly specify verification mechanisms for agricultural produce quality standards.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the parties shall clearly specify phenomena that might cause the deviation of quality of the agricultural produce from the agreed quality and effects thereof on the enforcement of the agricultural production contract. particulars shall be prescribed in the Ministry Directive;

3/ The agricultural production contracting parties shall clearly specify packaging, labeling standards and expenses of packaging, if any, and the party that shall bear related;

**13. <u>Input Supply and Payment</u>**

1/ The parties shall clearly specify, in their agricultural production contracts, the type, quality, quantity, time and place of delivery, mode of transportation, and price of input to be provided by the Contractor.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the price of the input to be provided by the Contractor shall not be higher than the prevailing local market price of same or similar input at time of delivery.

3/ The Contractor may pay in advance cash or through other mode of payment to the Producer for input purchase or other expenses; such payment, however, shall not be higher than the agreed total price of the agricultural produce.

CamScanner

**፲፬. የግብርና ምርት ርክክብ**

ተዋዋይ ወገኖች የግብርና ምርቱን የማስረከቢያ ቦታ፣ ጊዜ፣ የማጓጓዣ ዓይነትና የወጪ አሸፋፈን መወሰን ይገባቸዋል፡፡

**፲፭. መብቶችንና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ**

የግብርና ምርት ውሉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተዋዋይ ወገኖች፦

፩/ በውሉ ድንጋጌዎች የሚያገኙዋቸውን መብቶች ማስተላለፍ አይከለከሉም፣

፪/ በውሉ ድንጋጌዎች የሚገቧቸውን ግዴታዎች ለማስተላለፍ የሚቻለው የሌላኛውን ተዋዋይ ወገን ፈቃድ ካገኙ ብቻ ነው፣

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተደነገገው መሠረት ግዴታን የማስተላለፍ ስምምነት ካለ ሥልጣን በተሰጠው አካል በኩል መፈፀም አለበት፡፡

**፲፮.ማበረታቻ ስለማግኘት**

የግብርና ምርት ተዋዋዮች የመድን ዋስትናን፣ መጠነ ሰፊ የገበያ ትስስር፣ካፒታል፣ የግብር ክፍያ ቅነሳ ወይም የእፎይታ ጊዜ፣ የእርሻ መሳሪያዎች ድጋፍ እና ሌሎች ማበረታቻዎች በሶስተኛ ወገን ሊመቻችላቸው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አራት

## የግብርና ምርት ውል ግዴታዎችን መወጣት ስላለመቻል

**፲፯. ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል**

፩/ ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሊባሉ የሚችሉ ድንገተኛ ክስተቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

ሀ) ስራውን በቀጥታ ራሱ ከሚሰራ አምራች በኩል ፅኑ ህመም፣

ለ) ከመጠኑ ያለፈ ወይም ያነሰ ዝናብ ፣ጎርፍ፣

ሐ) በጣም ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ሙቀት ፣

መ) እሳት አደጋ፣

ሠ) የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም ናዳ ወይም የመሬት መንሸራተት፣

**14. Delivery of Agricultural Produce**

The parties shall specify place and time of delivery, mode of transportation, and the party that covers the cost of delivery of the agricultural produce in their Contract.

**15. Transfer of Rights and Obligations**

Without prejudice to provisions of the agricultural production contract, parties:

1/ shall not be deprived to transfer their rights stated subject to contract terms;

2/ shall only transfer their obligations under the contract upon the consent of the other party;

3/ According to the provision of Sub-Article (2) of this Article, the transfer of obligation shall be done through responsible appropriate authority.

**16. Acquiring Incentives**

Contracting Parties may acquire incentives like insurance, wide scale of market linkage, capital, tax holiday or relief, farm machinery support and other incentives from a third party. particulars shall be prescribed by a Regulation of the Council of Ministers.

## PART FOUR

## NON-PERFORMANCE OF CONTRACT OBLIGATION

**17. Force Majeure**

1/ The following unexpected phenomena canbe considered as force majeure:

a) serious illness of the producer, if he himself is responsible to perform activities;

b) extreme high or low rainfall, flood;

c) extreme low or high temperature;

d) fire accident;

e) earthquake or landslide;

CamScanner

ረ) ከአምራች ግለሰቡ በተጨማሪ ተፅዕኖ የሚፈጥር ሰው ሰራሽ አደጋ፡ እና

ሰ) ከቁጥጥር በላይ የሆነ የእንስሳት ወይም እፅዋት በሽታና ተባይ ወረረሽኝ ክስተቶች ናቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩት ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ተብለው ሊወሰዱ የሚችሉት በውል በተጠቀሰው የምርት ዓይነት ላይ ያስከተሉት የጉዳት መጠን አምራቹ የገባውን ግዴታ በውሉ መሠረት መፈጸም የማያስችለው ስለመሆኑ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ወይም አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ ከሆነ ነው፡፡

፫/ የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች በአስመራችና በአምራች በኩል ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሊባሉ የሚችሉ ክስተቶችን እና ውጤቶቻቸውን በግብርና ምርት ውላቸው ላይ ለይተዉ ሊያስቀምጡ ይችላሉ ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) በተገለፀው ከግብርና ምርት ተዋዋይ ወገኖች ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል በተፈጠረ ጊዜ አንዱ ለሌላው ወገን ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ ዝርዝሩ በሚኒስቴሩ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭/ የግብርና ምርት ውሉን ለመፈፀም ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል በተከሰተ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖች የግብዓት እና ሌሎች ወጪዎችን አሸፋፈን በተመለከተ በውላቸው ሊያካትቱ ይገባል፡፡

## ፲፰. የመድን ዋስትና

የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች፡-

፩/ ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ውሉ እንዳይፈጸም ለሚያደርጉ አደጋዎች የመድን ዋስትና ሽፋን ለመግባት ሊስማሙ ይችላሉ፡

፪/ የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች የመድን ዋስትና ሽፋን ለማግኘት የተስማሙ እንደሆነ በስምምነታቸው የመድን አረቦን ክፍያ የመፈጸም ግዴታ የሚወስደውን ወገን መለየት አለባቸው፡

f) man-made accident affecting more people including the producer;and

g) extreme animal or crop disease or pest outbreaks.

2/ Causative events listed under Sub-Article (1) of this Article shall be considered to constitute force majeure where such causative events prevent a Producer from undertaking his obligations, if they are confirmed by the two parties' agreement or verified by the appropriate authority.

3/ Parties to the Agricultural Production Contract may specify the causative events that can be considered as force majeure and the effects thereof.

4/ In occurrence of force majeure under Sub Article (1) or (2) of this Article, the party shall forthwith notify the other party and take reasonable measures to mitigate the adverse impact. particulars shall be determined by the Ministry Directive.

5/ The Parties may specify the party that bears the cost of input and other expenses for the amount lost in the agricultural production contract.

## 18. Insurance

Parties to Agricultural Production Contract may:

1/ Agree to obtain insurance against force majeure that prevent a party or the parties to the contract from undertaking his/their obligations;

2/ Where the parties to the agricultural production contract agree to obtain insurance, they shall specify the party liable for payment of the premium;

CamScanner

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለፀው ቢኖርም ሦስተኛ ወገን የመድን አረቦን ክፍያ እንዲሸፈን ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## የግብርና ምርት ውል ዘመን፣ ውሉን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር እና ውልን ስለማቋረጥ

### ፲፱. የግብርና ምርት ውል ዘመን

፩/ ተዋዋይ ወገኖች በውሉ የሚሸፈነውን የግብርና ምርትን የአመራረት ዘዴ ባገናዘበ መልኩ የውል ዘመን ይወስናሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀው ቢኖርም በባሕሪያቸው ልዩ የግብርና ምርት ውል ዘመን ለሚያስፈልጋቸው የግብርና ምርቶች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ሊወሰን ይችላል::

### ፳. የግብርና ምርት ውሉን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር

ተዋዋይ ወገኖች በሚከተሉት ምክንያቶች ውሉን ለማሻሻል ወይም ለመቀየር ይችላሉ፡-

፩/ የግብዓት ወይም የምርት ዋጋ በውል ወቅት ከሚገመተው በመብለጥ ወይም በማነስ ልዩነት የተፈጠረ እንደሆነ እና ይህም አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ እንደሆነ፣

፪/ የግብርና ምርት ዓይነትና መጠን ለመለወጥ የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ሲኖር፣

፫/ የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች ውላቸውን ለማሻሻል ወይም ለመቀየር በሚቀርብ የጽሁፍ ጥያቄ የተስማሙ እንደሆነ በዚህ አዋጅ ስለውል መመስረት የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

### ፳፩. የግብርና ምርት ውልን ስለማቋረጥ

፩/ ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ማቋረጥ ስለሚያስችላቸው ሁኔታዎች በግልፅ ማስፈር አለባቸው ፡፡

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the parties may agree to get their insurance premium from a third party.

## PART FIVE

## DURATION, RENEWAL OR ALTERATION; AND TERMINATION

### 19. Duration of the Agricultural Production Contract

1/ Parties shall state the duration of the contract taking into account the nature and production method of the agricultural produce covered in the contract;

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Ministry may determine, by a Directive, the duration of Agricultural Production Contract for agricultural produces with specific nature

### 20. Renewal or Alteration of the Agricultural Production Contract

Parties to the Agricultural Production Contract may agree to renew or alter their contract:

1/ When either input or agricultural produce price is beyond the anticipated price at the time of concluding the Contract and the same is verified by the appropriate authority;

2/ When Parties agree to change the type and quantity of agricultural produce;

3/ Where the Parties to the contract agree to renew or alter their contract, all formal requirements for the formation of the Contract under this Proclamation shall apply to effect the renewal or alternation of the contract.

### 21. Termination of the Contract

1/ Parties may stipulate the specific situations under which each party is entitled to terminate the Contract.

CamScanner

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሉን አንዱ ወገን ያለስምምነት ለማቋረጥ የፈለገ እንደሆነ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሌላኛው ተዋዋይ ወገን ላይ ለደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ ካሳ መክፈል አለበት፡የካሳ ስሌትን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## አለመግባባትን ስለመፍታት

### ፳፪. ያለመግባባት ሲከሰት የአፈታት ሂደት

ከውሉ ድንጋጌዎች ወይም ከውሉ ጋር በተያያዘ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ተዋዋይ ወገኖች፡-

፩/ በመጀመሪያ አለመግባባቱን በድርድር መፍታት አለባቸው፤

፪/ አለመግባባቱን በድርድር መፍታት ካልቻሉ አግባብነት ያለው አካል ወይም በሁለቱ ወገኖች በሚመረጥ ገለልተኛ ወገን በግልግል ዳኝነት ወይም በሽምግልና ሊስማሙ ይችላሉ፤

፫/ አለመግባባቱን በግልግል ወይም በሽምግልና ለመፍታት ያልቻሉ እንደሆነ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

## ክፍል ሰባት

## የግብርና ምርት ውል አዋጅ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

### ፳፫. የሚኒስቴሩ ወይም በክልል አግባብነት ያለው አካል ሥልጣንና ተግባር

፩/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ በተደነገገው አግባብ የግብርና ምርት ውልን በሚመለከት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) ለግብርና ምርት ውሎች አስፈላጊ የሆኑና በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች የተጠቀሱ መመሪያዎችን እና ሞዴል ውሎችን አዘጋጅቶ ያሰራጫል፤

2/ Without prejudice to provisions of Sub-Article (1) of this Article, a Party to the agricultural production contract that decides to terminate the contract shall compensate the other party for the damage arising from the termination of the contract; Calculation of compensation shall be set by the Council of Ministers Regulation.

## PART SIX

## DISPUTE RESOLUTION

### 22. Dispute Resolution Procedures

Parties to agricultural production contract may resolve dispute through the following resolution mechanism:

1/ The parties shall first settle their dispute amicably between themselves through negotiations;

2/ Where the Parties fail to reach an amicable settlement by themselves through negotiations, they may resort to mediation by a third party or settle the matter by arbitration;

3/ Where the Parties fail to resolve the dispute through mediation or arbitration, they may lodge a complaint to a court of law with appropriate jurisdiction.

## PART SEVEN

## DUTIES AND POWERS OF EXECUTORS OF THE PROCLAMATION FOR AGRICULTURAL PRODUCTION CONTRACTS

### 23. Powers and Duties of the Ministry and Appropriate Regional Body

1/ The Ministry of Agriculture shall have the following powers and duties regarding agricultural production contracts:

a) Develop and distribute Directives and templates of agricultural production contracts as prescribed under this Proclamation;

ለ) በግብርና አምራቾች እና አስመራቾች መካከል ግንኙነት እንዲፈጠር ያስተባብራል፣

ሐ) ለአምራቾች፣ ለአስመራቾች እና ለሦስተኛ ወገን የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፣

መ) ከግብርና ምርት ውሎች የሚነሱ አለመግባባቶችን አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚፈቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ሠ) የግብርና ምርት ውሎችን ያስተዋውቃል፣ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፣

ረ) አግባብነት ያላቸውን የተመዘገቡ ውሎችንና ሰነዶችን ይይዛል፣

ሰ) አገራዊውን የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ተግባራትን የሚያስተባብር የሥራ ክፍል ይሰይማል ወይም ያደራጃል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ለማስፈፀም ሚኒስቴሩ ከሌሎች አግባብነት ያላቸው የፌደራል እና የክልል የመንግስት አካላት እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ የልማት ድርጅቶች ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል::

፫/ ሚኒስቴሩ እንደ አስፈላጊነቱ ሥልጣንና ተግባራቱን አግባብነት ላላቸው የፌደራልና የክልል መንግስታት አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል::

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሱት በተጨማሪ በክልል ደረጃ ግብርናን አስመልክቶ ሥልጣን የተሰጠው አካል እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በክልል ደረጃ ሕግ ሊያወጣ ይችላል::

፭/ የዚህን የግብርና ምርት ውል አዋጅ ለማስፈፀም የሚችል አግባብ ያለውን የክልል አካል የክልል መንግስት ሊሰይም ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፬. ተፈጻሚነት ያለው ሕግ

በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

b) Create linkages among agricultural producers and contractors;

c) Provide advisory services to producers, contractors and third parties;

d) Facilitate the resolution of disputes arising from agricultural production contracts in accordance with the relevant provisions of this Proclamation;

e) Creates awareness on agricultural production contracts, provide fertile environment, play a coordination role;

f) Register agricultural production contracts and documents of relevant records;

g) Organizes or nominates a national coordination department responsible for agricultural production contract activities.

2/ In discharging its powers and duties under Sub-Article (1) of this Article, the Ministry shall cooperate with and coordinate other relevant Federal and Regional government and non-government agencies.

3/ The Minjstry may, as appropriate, delegate its powers and duties to other relevant federal and regional institutions.

4/ In addition to the duties provided under Sub-Article (1) of this Article, the appropriate regional body responsible for agriculture development may institute additional duties by law for the best implementation of this Proclamation.

5/ Each Regional State may designate an appropriate regional body that executes this Proclamation of the agricultural production contract.

## PART EIGHT

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 24. Applicable Law

Provisions of the Civil Code shall be applicable to matters not provided in the provisions of this Proclamation.

**፳፭. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በአዋጁ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**፳፮. ደንብና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም መመሪያዎችን ያወጣል።

**፳፯. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**25. Inapplicable Laws**

No law or customary practices shall, in so far as they are inconsistent with this Proclamation, have effect on matters provided by this Proclamation.

**26. Power to Issue Regulations and Directives**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation or Regulations issued pursuant of Sub-Article (1) of this Article.

**27. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force upon the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Abeba, on this 6th day of July, 2023.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**



CamScanner